**መስከረም 3 ቀን 2018 ዓ/ም**

**ቀሲስ አስተርአየ**

***“የወቅቱ የሕዝብ ህልውና ትግል ተጠናክሮ በመቀጠል ለአሸናፊነት እንዲበቃ የሲቭል ማህበራት ሚና”*** ***በሚል የምኒልክ ሰፋሪ እያሉ ሕዝበ ክርስቲያን ካረዱና ቤተ ክርስቲያን ካቃጠሉ እነ አቶ ጀዋር በሚሰበሰቡበት መድረክ ለምን ቀረብክ ? ብላችሁ የወቀሳችሁኝን ወቀሳ ተቀብየዋለሁ፡፡ ግብዣውን ተቀብየ ለመቅረብ ላለምቅረብ ከራሴ ጋራ  ታግያለሁ፡፡***

***“መንፈስን አታጥፉ ትንቢትን (መናገርን) አትናቁ፡፡ ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ ከማናቸውም ክፉ ነገር ራቁ”(1ኛ ተሰ 5፡19_22) በምትለው ሐዋርያዊት ትውፊት በመመራት ያየሁትንና የሰማሁትን በአብነቱ ትምህርት እመዝነዋለሁ፡፡ ሰው በሚሰጠኝ ርእስ ተመርቼ እንድናገር ያብነቱ ትምህርት አይፈቅድልኝም፡፡ የቅስና አንደበቴ የፖለቲካ ጎርፍ የቀደደው ቦይ አይደለም፡፡***

***ለኢትዮጵያ ሕልውና በሚደረገው ስብሰብ እንድናገር ስጠየቅ የተሰጠኝ 13 ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ እምቢ ማለት በቤተ ክርስቲያናችን ክልክል ነው፡፡  ለንግግር ስጋበዝ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በተሰጠኝ የሰአት ገደብ ተገቢውን እውነት መመስከር ግዴታዬ ነው፡፡ አንድ ያብነት ተማሪ ቄስ በሕዝበ ክርስቲያኑ ህልውና ላይ የሚንጸባረቀውን ትቶ ሰው በመረጠለት ርእስ የሚናገር ከሆነ፡ ኦርቶዶክሳዊት መርሆ “በነፋስ የሚነዳ ተፍገምጋሚ ገለባ ነህ! ” ብሎ ቅስናውን ያፈረስክ ብሎ ከአውደ ምሕረቱ እንደሚያሽቀነጥረው አውቃለሁ፡፡ የነበረኝ ምርጫ “ኢትአብአነ እግዚአ ውስተ መንሱት” ብየ መጸለይ ነበር፡፡ እኛ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ፈተና በሌለበት ወቅት “ኢትአብአነ እግዚአ ውስተ መንሱት” እያልን የምንጸልየው  ይህን የመሰለ አጥብቂኝ ፈታኝ ቅጽበት ሲገጥመን እንድትመራን ነው፡፡***

***በአባትነቴ እንድናገር የተሰጠኝ ርእስ “ስለ ሀገር ሕልውና ሀሳብ ማቅረብ ነው፡፡ የተጋበዝኩትም በቅጽል ስሜ አባት ተብየ ነው፡፡ የጋበዘኝ ወገን እኔ የምከተለውን እምነት ቢከተልም ባይከተልም የኦርቶዶክስ አባትነቴን ተቀብሏል፡፡ የጋበዘኝም አባት ብሎ በግብር ቅጽሌ ነው፡፡ የአባትነትን ተልእኮየን በተጠራሁበት ግብር ቅጽሌ መወጣት ነበረብኝ፡፡***

***“ማንም ከታናናሾች ላንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሀ ብቻ በደቀ መዛሙርት ስም  የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አትጠፋበትም”(ማቴ 10፡42) እንዳለው የአብነት ድርቀት ባየለበት በዚህ ዘመን ስጋበዝ፡ በተጋበዝኩበት አባት በሚለው ግብር ቅጽሌ በቅኔ ዘረፋ መንገድ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በሆኑት አብነት አባቶቼ ስም ይህችን ቀዝቃዛ የጽዋ ውሀ የተጠሙ ለመሰሉኝ ወገኖቼ አቀረብኩላቸው፡፡***

**ጳጉሜ 1 ቀን 2017 ዓ/ም**

# አብነት በድርቅ በተመታበት ዘመን የቀረበች ቀዝቃዛ የጽዋ ውሀ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማሕጸኗ ሲያድር ቅድስት ድንግል እመቤታችን "በክንዱ ብርቱ ስራ ሰርቷል፡፡ በልባቸው ሐሳብ የሚታበዩትን በትኗቸዋል። ገዥወችን ከዙፋኑ አወርዷቸዋል። ትሑታንን ክፍ ከፍ  አደርጓል  የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቧቸዋል ሐብታሞችን ባዷቸውን ሰዷቸዋል"(ሉቃ 1፡52_53) ብላ የተናገረችበት ረድኤት ከዓሕጸ ሕሊናና ልሳን እንዲጠብቀኝ አምኜ በኢትዮጵያዊው አብነት ትምህርት የተቀረጸውን ንግግሬን እጀምራለሁ፡፡

አብነት በጠፋበት በዚህ ዘመነመንሱት፡ በመካከላችን ተገኝታችሁ ስለ ሕዝባችን ሕልውና ሐሳባችሁን ግለጹልን ብላችሁ በጠየቃችሁት መሠረት ለሀገራዊ ግንባታ የተሻለ ምትክ የማይገኝለትን ያብነቱን ምክር እንዳካፍላችሁ በመምህር ንዋይ አማካይነት ወደናንተ የላከኝን የካህናቱን ጉባኤ አምሰግናለሁ፡፡

ኩለንተናዊት ቤተ ክርስቲያናችን የኢትዮጵያዊነትን ሕልውና ለዘመናት ስታስጠብቅባቸው ስለነበሩት፡ እናንተ በሐሰት ትርክታችሁ ስላፈራረሳችኋቸው የኢትዮጵያ ሕልውና መሠረት ስለ ሆኑት እሴቶች የማቀርበውን ምስክርነት ለመስማት ፈቃደኞች በመሆናችሁ አምሰግናችኋለሁ፡፡

ለምስክርነት እራሴን የማቀርበውም ምትክ የማይገኝላቸውን እሴቶች ያስተማሩኝን መምህሮቼን ወክየ ነው፡፡ የማቀርበውም ምስክርነት በነ ቅዱስ እስጢፋኖስ ትመራ በነበረችው በቅድሞዋ ቤተ ክርስቲያን መርሆ ላይ ስለተመሰረቱት ምትክ ስለማይገኝላቸው እሴቶች ነው፡፡

በሐዋርያት ዘመን የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ከገጠማት የከፋ ስደትና እልቂት የዛሬይቷን ቤተ ክርስቲያናችንን እንደገጠማት በሁላችሁም ዘንድ ግልጽ ነው፡፡ ይህን ዘመን የከፋ የሚያደርገውም ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችንን የገጠሟት ጳዋትወ መከራወች ሐዋርያትን ከገጠሟቸው መከራ እጅግ የከፉ በመሆናቸው ነው፡፡ ዛሬ በቤተ ክርስቲያችን አቡኖች እንደሚታየው ህዝብ እየበላ የሚያስበላ አቋም የነበረው በሐዋርያት መካከል አንድም እንኳ አልነበረም፡፡

በዚያ ዘመን ከሐዋርያት እሴቶች ጋራ የሚጋጭ እጅግ ኃይለኛ አቋም የነበረው ሊበርጢኖን (የነጻነት ስብስብ) የሚባል (የሐ 6፡9) ስብስብ ሐዋርያትን ገጥሟቸዋል፡፡

የናንተ ስብስብ  ቤተ ክርስቲያናችን የኢትዮጵያን ሕብረተ ሰብ ስትገነባባቸው ከነበሩት እሴቶች ጋራ በተጋጨ አቋሙ እነ ቅዱስ እስጢፋኖስን ከገጠማቸው  የከፋ መከራ ገጥሟታል፡፡ ይህን ስብስብ (ሊበርጢኖን) ቅዱስ እስጢፋኖስ እንዲህ ሲል ተጋፍጦታል፡፡

*"እናንት ልባችሁና ጆሯችሁ ያልተገረዘ  አንገተ ደንዳኖች ልክ እንደ አባቶቻችሁ መንፈስ ቅዱስን ሁሉጊዜ ትቃውማላችሁ ከነበያት መካከል አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማን አለ? በመላእክት አማካይነት የተቀበላችሁትን ሕግ አልጠበቃችሁም"*(የሐዋ 7፡51_53)

ሊበርጢኖን የተባለው ስብስብ የቅዱስ የአስጢፋኖስን ተግሳጽ ከመቀበል ይልቅ አሴረበት፡፡ ሴራውን ያልተረዳውን ህዝብ አንሳስቶ አዘመተበት ፡፡ በመጨረሻም ገደለው፡፡ <u>ዛሬ የማቀርብላችሁ ምስክርነት እስጢፋኖስ የተገደለበትን ሴራ የሚያሳስብና እንዳይደገም የሚያስተምረው በአብነቱ ትምህርት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡</u>

እስጢፋኖስ የተገደለበት ሴራ በቤተ ክርስቲያናችን እንዳይደገም የምንማረው ትምህርት አብነት ይባላል፡፡ <u>መምህራኑ የሚታወቁት ያብነት መምህራን በመባል ነው፡፡ አብነት ሁለት ትርጉሞች አሉት፡፡ አንዱ አባትነት ማለት ሲሆን፡- ሁለተኛው ፈዋሽ ፍቱን መድኃኒት ማለት ነው፡፡</u>

በጥንቱ ኢትዮጵያዊ ስርአተ ትምህርት የፊደላትን ዘሮች አውቀን ማንበብ መረዳት የሚያስችለንን ዳዊት ከደገምን በኋላ፡ ወደ አብነቱ  ትምህርት ስንሻገር ያብነቱ መምህራን የሚቀጥለውን ቅድመ ዝግጅት ይሰጡናል፡፡

እንደምታውቁት የአብነቱ ትምህርት ስንማር የዕለት ምግባችችንን የምናገኘው ካካባቤው ሕዝብ "በእንተ ስማ ለማርያም" እያለን በመለመን ነው፡፡ ከየመንደሩና ከየቤቱ የምንሰበስበው ምግብ አንድ አይነት አይደለም፡፡ ከድሀ እስከ ባለጸጋ ያለው ህዝብ ራሱ ከሚመገበው ከስንዴ ከሽንብራ ቆሎ ከባቄላ እንግርግብ ጀምሮ እስከ ደሮ መረቅ ንክኪ ያለውን ይሰጠናል፡፡

ከተለያየ ቤት እየሰበሰብን የምንሸከምባት እቃ አንዲት ናት፡፡ ኮፌዳ ወይም አኩፋዳ ትባላለች፡፡ ያብነት መምህራን ከቁጠማ ወይም ከሰሌን ራሳችን እንድንሠራት ያደርጉናል፡፡ በሰምና ወርቁ ቅኔ ትምህርታችን ኮፌዳዋ ኢትዮጵያን ወክላ ኢትዮጵያን ገላጭ ሰም ትሆናለች፡

ከተለያዩ ቤቶች  በኮፌዳችን የምንሰበስበው የተቀላቀለው ምግብ  ውጥንቅጥ ይባላል፡ ፡ ተወናቅጦ የተቀላቀለው ምግብ በደም ባጥንት ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለውን የተወናቀጠውን ሕብረተ ይወክላል፡፡ የተቀላቀለውን ምግብ ሰብስባ የያዘችው ኮፌዳ ብትቀደድ በውስጧ ያለው ውጥንቅጥ እንደሚበተን የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ቢደፈር በውጥንቅጥ የተገለጸው ሕብረተሰብ ይበተናል ብለው አስተምረውናል፡፡

ወደ ቅኔው ይዘት ዘልቀን ስንሔድ ከሰምና ወርቅ ጀምሮ የኢትዮጵያዊነትን እሴቶች ወደተሸከሙት ወደ ብዙ የቅኔ አይነቶች ላይ ያደርሰናል፡፡

ከብዙ መንገዶች ሁለቱን ኅብርና ሠረዝ የተባሉትን እሴቶች ለመግለጽ የቅኔ መቁጠሪያ ፊደላችን (ጉባዔቃና) የያዘቻቸውን እሴቶች በሰፊው አካቶ የያዛቸውን መወድስ ወይም ኩልክሙ የሚባለውን ይዘት ባጭሩ ለመዳሰስ እሞክራለሁ፡፡

የቅኔ ፈደል መቁጠሪያች ጉባኤቃና አንድ ኢትዮጵያዊ ካንድ አባት አብራክ ካንዷት እናት ማሕጸን ከሁለት አካላት ፈልቆ ባባቱ በኩል ከሁለት ወንድና ሴት አያቶች ባናቱ በኩል ከሁለት ወንድና ሴት አያቶች የአራት ሰወች ድምር ውጤት በመሆን ባንድ ነጠላ ሰውነቱ አራቱን ሐረጎች ሕብር ማድሩጉን ታመለከታለች። ከመደበኛው ስምንት ቤቶች ሲረዝምና ሲያጥር "ኩልከሙ" ይባላል። ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሉ ለማመልከት ሁላችሁም ማለት ነው።

ስታሊንን nation nationality ብሎ የተናገረውን "ብሄር ብሄር ሰቦች" ብላችሁ ወደ ኢትዮጵያ ጎትታችሁ በማምጣት ሕብረተ ሰቡን እስክትበታትኑት ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕብርነቱን ሳያጣ አንድ ሕዝብ ሆኖ በቅኔያችን እንደተገለጸው ባንዲት ኢትዮጵያ የሚኖር በሕብረተሰብነት ይጠራ ነበር።

ሕብር ማለት የተደራረበ ትርጉም ያዘለ አንድ አካል የሚገልጽ ግሥ ስለሆነ እያንዳንዱ ኢቶዮጵያዊ የመላ ኢትዮጵያውያንን ደምና ሰውነት የተሸከመ ኅብረሰውነት ይሆናል። ከጽንፍ እስከ ጽንፍ አንድ ኅብረተ ሰብ ይባላል።ዜጋ የሚለው ትርጉም የሚገልጸው ተጎራብቶ የመኖርን ስሜት ስለሆነ ከሕብረተ ሰብነት የራቀ ወደ አጎራባች አገሮች ያዘነብላል ይላሉ።

ሕብረተ ሰባዊነትን ካፈረሱት አንዱ የነበሩት አቶ መለሰ ባንድ ወቅት ሌላውን ሕብረተሰብ ቀላጭ ሰም በማድረግ የትግራይን ሕዝብ አቅላጭ ወርቅ አድርገው በመናገራቸው ኢትዮጵያዊውን ኅብርነት መስበራችርውን ባወጁት ጊዜ ያብነቱ መምህራንና ተማሪዎች ደንግጠናል። የዚያ አካባቢ አባቶች መገሰጽ ሲገባቸው አብነትነታቸውን ዘንግተው የወያኔ የፖለቲካ ጎርፍ በቀደደላቸው ቦይ መፍሰሳቸው እጅግ በጣም አሳዝኖናል። የወያኔ የፖለቲካ ጎርፍ በቀደደላቸው ቦይ መፍሰሳቸውን አሁንም አጠናክረው መቀጠላቸው ተመልካቹን ሁሉ በማስገረም ላይ ነው።

አባቶቻችን የሰሯቸው ሕብረተ ሰባውያን እሴቶች በከፋፋይ ጠላት ህዝቡ ተከፋፍሎ የኢትዮጵያ ሕልውና እንዳይናጋ እድል ላለመስጠት ነበር እንጅ፡ አንዳንድ በዋለልኝ ተጎትቶ የገባውን የስታሊን ጥራዝ ነጣቂወች እንደሚሉት ሕብርነትን ለመጨፍለቅ አልነበረም።

ላለመጨፍለቅ ቤተ ክርስቲያናችን ያደረገችውን ጥንቃቄ የሕዝቡን ባሕል ጥርግርግ አድርጋ ባለማጥፋቷ ለማሰወረር ያልተመቻቸው የውጭ ሰባኪወች sincritsized የሚል አሽሙረኛ ቅጽል ሰጥተዋታል። ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ የዚህ ስብስብ ተካፋዮች ልጆቻችሁን ከግእዙ ፈደል አሸሽተችሁ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችሁ ሲዋጓቸው ወደነበሩት ወደላቲን ፈደል አትከቷቸውም ነበር።

ምናልባት አሁን ተጸጽታችሁ ንስሐ ገብታችሁ የናዳችኋቸውን እሴቶች በመገንባት ለበደላችሁት ኅብረተ ሰብ የንስሐ ካሳ ማቅረብ ከፈለጋችሁ፡ በተዛባ ትርክታችሁ ያፈረሳችኋቸውን በተለምዶ ሲነገሩ የምትሰሟቸውን እሴቶች ልጠቁማችኋለሁ።

በደበዘዘ ትርጉም ሲነገሩ የምትሰሟቸው ያፈረሳችኋቸው እሴቶች በስድስት ቃልት የተጎነጎኑ ናቸው። እነሱም 1ኛ፡ባለ፤ 2ኛ ደም፡ 3ኛ አገር፤ 4ኛ ጋራ፡ 5ኛ አምጣ፡ 6ኛ ቤት ናቸው። አምስቱ ቃላት ባለ የምትለውን ቃል ትራስ በማድረግ የህብረተ ሰቡን ስሪት የሚገልጹ ናቸው። እንደሚከተለው ይብራራሉ።

1ኛ ባለደም፡ ይህም ማለት ከላይ በህብርነት እንደተገለጸው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከመላው ሕብረተ ሰብ ደም ተካፋይና ተሳታፊ ነው። በደም ያልተነካካ ባእድ የለም ሁሉም ባለደም ነው ማለት ነው። ያስኳለውን ትምህርት ይዘው የመጡት መምራን ጽንሰሐሳቡን ገልብጠው በተሳሳተ ትርክት በበቀልና በመገዳደል ላይ ተከሉት።

2ኛ ባለአገር፡- እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለቸው ኢትዮጵያ አገሩ ናት። ያስኳለውን ትምህርት ይዘው የመጡት መምራን ጽንሰሐሳቡን ገልብጠው በተሳሳተ ትርክት ተማሪወቻቸውን እናንተን ከባለአገርነታችሁ ቆርጠው ከገጠሩ ሕዝብ ለይተው ባለአገር የሚለውን ቃል አስንቆና አርቆ በሚያሳይ በተሳልቆ ጽንሰ ሐሳብ ላይ ተከሉት።

3ኛ ባለቤት፡- እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለው የኢትዮጵያ ገጸ ምድር የራሱ ስለሆነ በፈለገበት ሄዶ ቤት ሰርቶ ንብረት አትርፎ ቢኖር ጠያቂ የለውም። በመላዋ ኢትዮጵያ ውስጥ በኄደበት ሁሉ ባለቤት ነው። እናንት ያስኳላ ተማሪወች ባለቤትነቱን ክዳችሁ በቤቱ ላይ ዘመታችሁ ። አፈረሳችሁበት። አፈናቀላችሁት። ስደተኛ አደረጋችሁት።

4ኛ ባለጋራ፡-ባለጋራ የሚለው ቃል አጋርነትን ተጋሪነትን ተካፋይነትን ተደጋጋፊነትን ገላጭ ነበር። እናንተ ይህን ጽንሰ ኀሳብ ቀይራችሁ በመጠላላት በመገፋፋትና በመጠራጠር ተከታችሁ ሕብረተ ሰቡን ሆድና ጀርባ አደረጋችሁት።

5ኛ ባለ አምጣ ማለትም ያለው ለሌለው የሚያመጣለትና በጎደለው የሚሞላለት የሚለዋወጠው ነገር እንዳለው የሚያሳየው ነበር። እናነተ ግን ትርጉሙን ቀይራችሁ በጠላትነት መንፈስ ተከታችሁ ሕብረተ ሰቡን እርስ በርሱ እንዲዘራረፍ አደረጋችሁት። ጭራሽ እንዳይገናኝ በክልል አቆራረጣችሁት።

በተሳሳተ ትርክታችሁ ከላይ ለተዘረዘሩት እሴቶች ዋና አመንጭና ተዋናይ በማድረግ አራት አይነት ብትሮች አዘጋጅታችሁ በአራት ማንነቶች

1ኛ ባማራነት

2ኛ በኦርቶዶክስ ክርስቲያንነት

3ኛ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲን

4ኛ በኢትዮጵያዊነት ላይ ዘመታችሁ።

ከኢትዮጵያ የመገንጠልን ዓላማ ይዛችሁ የወጣችሁበትን ህዝብ ወክላችሁ የቀረውን ህብረተ ሰብ አስተባብራችሁ የዘመታችሁበት አማራ፤ ጭፍጨፋ በዝቶበት ራሱን ለመከላከል

ተገዶ በፋኖነት እስኪደራጅ ድረስ ኢትዮጵያ እያለ በናንተ ከመጨፍጨፍ በቀር ከኢትዮጵያ የመገንጠል ሕልምም አሳብም አልነበረውም። አሁንም የለውም። ይህ መሆኑን እያወቃችሁ ራሱን ለመከላከል የሚያደርገውን ጥረት ቀይራችሁ በባንዳ ስም ፈረጃችሁት። ይህ ደግሞ ምድር ልትሸከመው የማትችለው ከሁሉም እጅግ የከፋ  በደል ነው።

ኃጥእ በደለኛ አድርጋቻሁ በአማራው ላይ የሰነዘራችኋቸው በትሮች ንክኪ ያለውን ሁሉ ኦሮሞውን ጉራጌውን ወላይታውን የትግራይን ሕዝብ ሳይቀር ጨፈጨፋችሁት። ብዙ በደል የፈጸሙትን አቶ ስብሀት ነጋና አቶ ጀዋር ለቃችሁ፣ ያፈራረሳችኋቸውን እሴቶች በመመስከራቸውና በኦርቶዶክስ ንክኪነታቸው አቶ ታዴወስ ታቶንና የመሳሰሉትን በማሰቃየት ላይ ናችሁ።

ባለማወቃችሁም ሆነ አውቃችሁ አንዳንድ ጊዜ ስለ አገር ግንባታ ስታወሩ ካፈረሳችኋቸው እሴቶች አንድ እንኳ ሳታወሱ በቀዳሚነት መንግሥት አዋቅራ በሶስቱ ሃይማኖቶች ማለትም በይሁዲ በክርስትና በስልምና እምነት ባህሏን መስርታ ከኖረቸው ከአገራችሁ እንዴት የምትጠቅሱት አታችሁ ለአገር ግንባታ የምትጠቅሷቸው ሁሉ በዓረብ አገርና በሌሎች አገሮች ያያችሏቸውን ነው።  አባቶቻችን በተቀደሱት እሴቶች እየተመሩ ለነጻነታቸው ምሳሌወች ከሆኑላቸው በቅኝ ገዥወች ይሰቃዩ ከነበሩት አኅራባች ዜጎች በታች ወደቃችሁ።

ከናንት በፊት የነበሩት ደርግ ኢሐፓ ኢጫት ኢማለዲህ በመብባል ተከፋፍለው ከተጨራረሱትና ማጨራረሱን ለናንትና ለብልጽግናው መንግሥት ካወረሱት  የፖለቲካ አባቶቻችሁና አሁን ደግሞ በኦሮሞ ስም የጨበጠውን በትረ መንግስት ወደበትረአመጻነት ቀይሮ ሕዝቡን በመደብደብ ላይ ካለው መንግሥት ጋራ ባለአምጣወችና ባለጋራወች ናችሁ።

ባለአምጣነታችሁና ባለጋራነታችሁ ከናንት በፊት ከነበሩት ከደርግ ከኢሐፓ ከኢጫት ከኢማለዲህ ከወያኔና ከብልጽግናው መንግሥት ጋራ ብቻ አይደለም። በዘመናችሁ ካሉት አባቶቻችን የምትሏቸው እናንተ በቀየሳችሁላቸው ቦይ ከሚኖሩዱት አቡኖች ጋራ ነው።

“ከመ ነፍስ ተዐቢ እምሥጋ፡ ክህነት ተዓቢ እመንግሥት” ብሎ መጽሐፈ ቀኖናችን እንደሚነግረን፡- ማለትም ነፍስ ከለበሰችው ሥጋ እንደምትልቅ፡ ባንድ አገር ከሚገኘው መንግሥትና ባካባቢው ካሉት ልሂቃን በዚያው አካባቢ ያለው ቤት ክህነት በመንፈስ በሞራል በጥበብ በማስተዋል ይልቃል።

እናንተ አባቶች ከምትሏቸው ከፓትርያርኩ ጀምሮ የቅዱስ ሲኖዶስ አባልነን የሚሉና እስከ ገጠር ያሉት ሁሉ ካህናት ሰባኪወች በቅድስናቸው በብጽዕናቸው ህብረተ ሰቡ ተስማምቶ ከዘረጋው ምድራዊ ሕግ  በላይ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል። እነሱ ባይገሉም ባይዘርፉም ሕዝብ ሲገደል ሲዘረፍ ዝም ካሉ በቀኖናችን መሠረት ካድራጊው የበለጠ ፍርድ ይጠብቃቸዋል።

"ነቅ ንጹሕ ዘእም አንቅእተ ሕግ ዝ ውእቱ ዜና ግብሮሙ ለሐዋርያት" ማለትም "ከንጹሕ ሕግ የመነጨውን ንጹሑን የሐዋርያት ተግባር እንመሰክራለን በተግባርትም እናውለዋለን" እያሉ በህዝብ ፊት ቆመው የሚያነቡትን በመካድ ከመጣው መንግሥት ሁሉ ጋራ በመተባበር ቆመው በማስገደል ላይ ያሉት አቡኖች ከቀኖናው ይልቅ እናንተን ስለሚሰሙ ቀኖናችን የሚሰነዝርባቸውን ፍርድ እንዲቀበሉ ብትነግሩልን ንስሀ ለመግባት ፈቃደኝነታችሁን ይጠቁመን ነበር፡፡

በቃላችሁ በንግግራችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ በፈጸማችሁት በደልና ሲራ በፈሰሰው ደም ምሬቱ ሲጨቀይ ፡፡ የሚፈሰው ደም ከሚፈልቁት ወንዞች ጋራ እየተቀላቀለ ሕዝቡ ሲጠጣው፡ የሚንፈሰው አየር የተቀላቀለውን ደምና ሥጋ ከመሬት እየጋፈ ባፍንጫው ሲግተው ፡ አፈር ትቢያ የሆነውን የወገን አካል ነፋሱ ቆሞ በሚሄደው ላይ በመበተን በቁሙ ሲቀብረው ዝም በማለታቸው፡ ህዝቡን እርም አብልተውታልና በወገን አፈር በቁማችን ስንቀበር ዝም ብለዋልና አቡኖቻችሁ ነን የሚሉ ሁሉ ከናንተ ይልቅ ከባዱን ፍርድ ሊቀበሉ ይገባቸዋል፡፡

በነገራችን ላይ ባይገርማችሁ ብዙ የተገደሉና በመገደል ላይ ላሉትና ለሚተርፈው ሕዝበ ክርስቲያን በፓትርያርክነት ቀኖናችን የሚቀበላቸው የታሰሩለትን የተሰቃዩለትን ሰማእት አቶ ታዴወስ ታቶን ነው፡፡

ከአቡነ ማትያስ ጀምሮ በዚህ ዘመን ያለን ካህናትና እናንተ ሁላችሁ ከብልጽግና መንግሥት ጋራ ተቆራኝታችሁ ወደ ሰማእቱ ታዴወስ ሄዳችሁ እሳቸው የሚሰጧችሁን ንስሐ በመቀበል የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚሰይመው ዳኛ እጃችሁን ብትሰጡና ፍትህ ቢፈጸም መሬት ትጽዳለች፡፡ አየሩም ይጸዳል ወንዞችም ይጠራሉ፡፡ ከዚህ የተሻለ ኢትዮጵያን የሚፈውስ ፍቱን አብነት የሚገኛ አይመስለኝም፡፡

ንስሀ ሳትገቡ በተቆርቋሪነት መፍትሄ አፈላላጊ ሆናችሁ ብትቀርቡ እባብ አይቶ በልጥ የሚደነግጠው የኢትዮጵያ ህዝብ ገና ሲያያችሁና ድምጻችሁን ሲሰማ ደንግጦ የሚሸሻችሁ ይመስለኛል፡፡ ያብነቱ ትምህርት ከዚህ የተሻለ ሌላ ፍቱን አብነት (መድኃኒት) እንዳለ አላስየኝም፡፡

"ማንም ከታናናሾች ላንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሀ ብቻ በደቀ መዛሙርት ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አትጠፋበትም"(ማቴ 10፡42) እንዳለው ቤተ ክርስቲያናችን ባባትነት ድርቅ በተመታችበት ዘመን በስብሰባችሁ ተገኝቼ አባት በሚለው ግብር ቅጽሌ በቅኔ ዘረፋ መንገድ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በሆኑት አብነት አባቶቼ ስም ይህችን ቀዝቃዛ የጽዋ ውሀ አቀረብኩላችሁ፡፡

በዚህ ኣይነት አቀራረቤ ጠላቶች ባልላቸውም ብዙ ወዳጆቼ ጳጳሳትና የቤተ ክህነቱ ቅጥረኞች የቀደም ፍቅራቸውን ነፍገውኛል፡፡ ጠልተውኛልም፡፡ እናንተ ግን ይህን ለመቀበል ፈቃደኞች

በመሆናችሁ እንደነሱ እንደማትጠሉኝ አምናለሁ። ከወሰናችሁልኝም 13 ደቂቃወች በላይ ትርፍ ደቂቃወች በመለገስ በትእግስት ስላዳመጣችሁኝ አምሰግናችኋለሁ።

እግዚአብሔር የሁላችንንም ዐይነ ልቡና ያብራልን።